ግንቦት 24 ቀን 2001 ኢ.ም.

# ወያኔ፣ «የህግ የበላይነት» እያለ የሚያናፋው ለምን ይመስላችሃል?

የወያኔ መሪዎች፣ አቶ መለስ ዜናዊ፣ አቶ ስብሃት ነጋ፣ አቶ በረከት ስምኦንና ሌሎቹ ንግግራቸውን የሚከፍቱትና የሚደመድሙት «የህግ የበላይነት» በሚለው ሃረግ ከሆነ ውሎ አድሯል፡፡ ለዚህም ምንጮቹ ሁለት ናቸው፡፡ አንደኛውና ዋነኛው የምእራባውያንን ቀልብ ለመሳብና «ዲሞክራቶች» ተብለው የኢኮኖሚውና የፖለቲካው ድጋፍ እንዳይቋረጥባቸው ነው፡፡ ይህም እቅዳቸው እስካሁን ሰርቶላቸዋል፡፡ ሁለተኛው ደግሞ፣ እነሱን የሚቀናቀኗቸውን የፖለቲካ የሞያና የብዙሃን ማህበራትን በህግ ሽፋን ለመምታት እንዲያመቻቸው ነው፡፡ ይሽኛውም እንደመጀመሪያው ሁሉ ተሳክቶላቸዋል፡፡ የወያኔን «የህግ የበላይነት» ኢትዮጵያችን አሁን ካለችበት የወቅቱ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማነፃፀር እንመልከተው፡፡ በማንም ሃገር ውስጥ የሃገሩ ህገ መንግስት የህጎች ሁሉ የበላይ ነው፡፡ ወያኔ «የኢትዮጵያ ህገ መንግስት» የሚለው አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ቁጥር-1 በ1987 ኢ.ም. ታትሞ ወጥቷል፡፡ እስቲ ወያኔዎች በየጊዜውና በየምክንያቱ ለሚወስዷቸው አስከፊ እርምጃዎች መከታ የሚያደርጉትን «ህገ መንግስት» በቅንጭቡ እንመልከተው፡፡

የወያኔ ህገ መንግስት አንቀፅ 8 ከቁጥር 1 እስከ 3 ስለ ህዝብ ሉአላዊነት እንደሚከተለው ይዘረዝረዋል፤ ያብራራዋልም፡፡

*1. የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች፣ የኢትዮጵያ ሉአላዊ ስልጣን ባለቤቶች ናቸው፡፡*
*2. ይህ ህገ መንግስት የሉአላዊነታቸው መግለጫ ነው፡፡*
*3. ሉአላዊነታቸው የሚገለፀው በዚህ ህገ መንግስት መሰረት በሚመርጧቸው ተወካዮቻቸውና በቀጥታ በሚያደርጉት ዴሞክራሲያዊ ተሳትፎ አማካይነት ይሆናል፡፡*

ይላል፡፡

እንግዲህ ልብ ብለን የወያኔን «ህገ መንግስት» ብንመለከተው፣ ግልፅ የሚያደርግልን፣ ኢትዮጵያ አንድ ሉአላዊ ሃገር ሳትሆን፣ ቀድሞ ነፃ ሃገር የነበሩ ዘጠኝ ብሄሮችና ብሄረሰቦችን የምታጠቃልል በአፍሪቃ ሰሜን ምስራቅ አካባቢ የምትገኝ ቦታ ነች፡፡

እነዚህም ሃገሮች በወያኔው «ህገ መንግስት» ውስጥ እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል፡-

1. የትግራይ ክልል
2. የአፋር ክልል
3. የአማራ ክልል

4. የኦሮሚያ ክልል
5. የሱማሌ ክልል
6. የቤኒሻንጉል/ጉሙዝ ክልል
7. የደቡብ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል
8. የጋምቤላ ህዝብ ክልል
9. የሃረሪ ህዝብ ክልል

በዚህ «ህገ መንግስት» መሰረት በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ቀድሞ ኢትዮጵያ ተብላ ትታዎቅ የነበረች አካባቢ ውስጥ በአሁኑ ወቅት በመላው አለም በሃገርነት የሚታወቁ ዘጠኝ ክልሎች ይገኛሉ። ህጋዊ ሰውነት ያላቸው፣ ሊከሱና ሊከሰሱ የሚችሉ፣ ከሌሎች ሉአላዊ ሃገሮች ጋር እንደ ሃገር ሊደራደሩና ስምምነት ሊፈራረሙ የሚችሉትም እነኝሁ በወያኔ «ህገ መንግስት» ውስጥ የተዘረዘሩት ዘጠኙ ክልሎች እንጂ ኢትዮጵያ የምትባለዋ ሃገር አይደለችም።

በወያኔ አባባል ከ1983 ኢ.ም. በፊት ለመቶ አመታት በመሳርያ ሃይል ተገደው ነፃነታቸውን ተገፈው፣ በጭቆና ተይዘው፣ መሬታቸውን ተነጥቀው ኢትዮጵያ በሚባል ቀንበር ስር የኖሩትን ህዝቦች አሁን ለነፃነታቸው እያዘጋጇቸው ነው።

የኢትዮጵያን ታሪክ ስንመረምር ግን የወያኔ ድምዳሜ መሰረተ ቢስ መሆኑን እንገነዘባለን። አብዛኛው ኢትዮጵያዊ የሚያውቀው ሃገራችን ከአምስት ሺህ አመታት በላይ ታሪክ ያላት ሉአላዊ ሃገር መሆኗንና በአካሏም ውስጥ አቅፋቸው የሚገኙት ልጆቿ የኢትዮጵያዊነት ታሪክ፣ ልምድና ወግ በጠቅላላው የጋርዮሽ ባህል ያላቸው መሆናቸውን ነው። ስለዚህም በማንኛውም የኢትዮጵያ ክፍለ ሃገር የተወለደ፣ የኢትዮጵያ ዜጋ እንጂ ሌላ ሊሆን አይችልም።

ወያኔዎች በህገ መንግስታቸው የሚለፍፉልን ግን «48 ነፃ የአፍሪካ አገሮች የአፍሪካ አንድነትን እንደፈጠሩት እና 194 ነፃ የአለም አገሮች የአለም ማህበርን እንደመሰረቱት፣ በተመሳሳዩ ዘጠኙ ነፃ ክልሎች (አገሮች) ኢትዮጵያ በሚለው የስም ጥላ ስር ተሰባስበዋል።» የሚለውን ጠማማ አንድምታ ነው።

ኢትዮጵያ የተባለው የተለያዩ አገሮች ስብስብም በአንድነት የሚቆየው ወያኔ እስከፈቀደ ድረስ መሆኑን የሚገልፅና አስፈላጊ በሆነም ጊዜ በስራ ለመተርጎም የሚያስችላቸውን አንቀፅ «ህገ መንግስት» እያሉ በሚጠሩት ፅሁፍ ውስጥ አስፍረውታል። ይህም በአንቀፅ 39 ውስጥ፣ «የብሄሮች ብሄረሰቦች፣ ህዝቦች መብት» በሚል ርእስ ስር እንደሚከተለው ተብራርቷል። «ማንኛውም የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰብ፣ ህዝብ የራሱን እድል በራሱ የመወሰን እስከመገንጠል ያለው መብቱ በማናቸውም መልኩ ያለገደብ የተጠበቀ ነው።» ይለናል።

«ህገ መንግስት» እያሉ በሚጠሩት ፅሁፍ ውስጥ በግልፅ እንደተቀመጠው፣ ኢትዮጵያ የሚለው ህብረት የሚኖረው ወያኔ በስልጣን ላይ እስካለ ድረስ መሆኑን መሪዎቻቸው በተደጋጋሚ ገልፀውልናል። ባጭሩ፣ ወያኔ የሚለው «እኛ እንገዛችሂለን፣ አለበለዚያ ትፈራርሳላችሁ።» ነው። ይህን ነው እንግዲህ «የህግ የበላይነት» እያሉ የሚያደነቁሩን።

ሌላው ደግሞ የሚገርመው፣ ህገ መንግስታቸውን ለመለወጥ ወይንም ለማሻሻል፣ የሚቻለው በነርሱው ፈቃድ ብቻ እንደሆነ በፅሁፍ ተረጋግጧል። በወያኔ ህገ መንግስት ውስጥ፣ በአንቀፅ 104 «የህገ መንግስትን ማሻሻያ ሃሳብ ስለማመንጨት» እንዲሁም በአንቀፅ 105 «ህገ መንግስቱን ለማሻሻል» በተሰኙት ርእሶች ስር፣ ለወያኔ መተማመኛ የሚሆኑ አንቀፆች ተቀምጠዋል። በጥቅሉ፣ ህገ

መንግስታቸውን ወያኔ ካልፈቀደ በስተቀር ተቀናቃኝ ቡድኞችም ሆኑ ወይንም የቡድን ተወካዮች ሊቀይሩት አይችሉም። ህገ መንግስታቸውን ለማሻሻል እንዲቻል ሃሳብ ቢቀርብ፣ ከዘጠኙ ክልሎች አንዱ እምቢ ካለ ሃሳቡ ውድቅ ይሆናል።

ወያኔ ለስሙ የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲ ግንባር (ኢህአዴግ) የሚለውን ድርጅት አቋቋቁሟል። ድርጅቱ ውስጥ ያሉት አራቱ አካላት፣ የአማራው፣ የኦሮሞው፣ የደቡብ ህዝብና ህዝቦች የሚሽከረከሩት በወያኔ ድርጅት ማለትም በትግራይ ህዝብ ነፃ አውጭ ግንባር ስለሆነ ወያኔ ቢያንስ 4 አለዚያም ከአራት በላይ ድምፅ አለውና ህገ መንግስታቸውን ያለፈቃዳቸው ማሻሻል የማይሞከር ጉዳይ ይሆናል። ህገ መንግስታቸውን አክብሬ ህገ መንግስታቸውን አሻሽለዋለሁ ለሚል ግብዝ እንጂ ለቆራጥ ኢትዮጵያዊማ ህገ መንግስት ለማሻሻልም ሆነ ለመቀየር የኢትዮጵያን ህዝብ ፈቃድ እንጂ የወያኔን አይጠይቅም።

በጥቅሉ ወያኔ «የህግ የበላይነት» ሲል፣ የራሱን «ህግ» ሙሉ በሙሉ ተቀበሉ ማለቱ እንደሆነ ግልፅ ሊሆንልን ይገባል። ህገ መንግስታቸውን ከተቀበልን ኢትዮጵያ የምትባል ሉአላዊ አገር እንደሌለች፣ ሉአላዊነት የተሰጠው ለዘጠኙ ክልሎች እንደሆነ፣ ወያኔም ያለገደብ እንደሚገዛን አምነን መቀበላችን ነው። ሌላ ምርጫ የለንም ማለት ሳይሆን ምርጫው አልተሰጠንም።

ስለዚህም ነበር የኢትዮጵያ መድህን ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ (መድህን) ገና ከምስረታው፣ ካለፈው አስራሰባት አመታት በፊት የወያኔ ስርአት ሊጠገን የማይችል ፀረ ኢትዮጵያ እንደሆነና፣ የወያኔ ስርአት እዲደመሰስ ለመላው የኢትዮጵያን ህዝብ ጥሪ ያቀረበው። አሁንም ቢሆን በህብረት ትግል የወያኔን ስርአት ጠራርገን መጣል ይኖርብናል።

ከአስራስምንት አመታት ትግል በሂላ የተማርነው፣ የትግላችን አካሄዱ ሁለት ዘርፍ ያለው መሆኑን ነው። በአንደኛ ዘርፉ የወያኔውን «ህገ መንግስት» የሚቀበሉ ግን «የወቅቱ የወያኔ መሪዎች ህገ መንግስቱን በአግባቡ ስራ ላይ አላዋሉትም።» ይሉና፣ «እኛ ስልጣን ብንይዝ ህገ መንግስቱን ዴሞክራሲያዊ እናደርገዋለን።» እያሉ የሚመፃደቁብን ሲሆኑ፣ በሁለተኛው ዘርፍ የሚመደቡት ደግሞ፣ ይህ «ህገ መንግስት» የተሰኘው ፅሁፍ፣ ፀረ ህዝብ፣ ፀረ ሃገር እና ፀረ ዴሞክራሲ አስተሳሰብ ስለሆነ በሙሉ ተወግዶ በእውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ስርአት እንዲተካ እንታገላለን።» የሚሉት ናቸው።

መድህን «ህብረት» ሲል ወያኔን በሌላ ወያኔ የመተካት ህልም አያልምም። የመድህን አላማ ወያኔን ለህዝብ ፍላጎት ተገዥ በሆነ አካል መተካት ነው። የመድህን አላማ በኢትዮጵያችን የምድር አቀማመጥ፣ የባህልና የኢኮኖሚ ልምድ ትስስርን ያገናዘበ ፌዴራል ሪፓብሊክ መመስረት ነው። የመድህን አላማ ኢትዮጵያ ሉአላዊ ሃገር መሆኗን ያለማወላወል ያመነ፣ የግል ዴሞክራሲን ያስቀደመና የቡድን ዴሞክራሲን ያረጋገጠ ስርአት መገንባት ነው። ከእንግዲህ መሆን ያለበት ትግል ኢትዮጵያን ለማዳን ስለሆነ አሁንም የምናቀርበው ጥሪ ስንመሰረት ጀምሮ ካሰማነው ጥሪ አይለይም። ተባብረን የወያኔን ስርአት በዴሞክራሲያዊ ስርአት ለመለወጥ ሁለ-ገብ ትግል እናካሄድ።

ሃገራችን ኢትዮጵያም በቆራጥ ልጆቿ ትግል በነፃነቷ ኮርታ በዴሞክራሲ አሸብርቃ ለዘለአለም ትኖራለች።

SEYOUMGELAYE_MEDHIN@WINDSTREAM.NET